

MEFCC

# ደን በኢትዮጵያ ሀገራዊ ገቢ ላይ ያለው አስተዋፅኦና ከ’ደን መጨፍጨፍና መመናመን ምክንያት የሚለቀቅ በካይ ጋዝ ቅነሳ’ (REDD+) ጋር ያለው ተያያዥነት

## ዋና ማጠቃለያ

UN-REDD PROGRAMME

Food and Agriculture Organization of the United Nations

UNDP
Empowered lives. Resilient nations.

UNEP

## መብት

© የተባበሩት መንግስታት የአካባቢ ፕሮግራም, 2017

የተባበሩት መንግስታት የአካባቢ ፕሮግራም አካባቢን የሚያበለጽጉ ተግባራትን በሚሰራቸዉ ስራዎቸና በዓለም ዙሪያ ያበረታታል። የእኛ የህትመት ፖሊሲ የተባበሩት መንግስታት የአካባቢ ፕሮግራምን የካርበን አሻራ ለመቀነስ መሰረት ያደረገ ነዉ።

## ማስተባበያ

በዚህ ዕትም ዉስጥ ያሉት ይዘቶቾ የተባበሩት መንግስታት የአካባቢ ፕሮግራምን ሃሳብ ወይም ፖሊሲ ላይመለከቱ ይችላሉ፡ ፡ በዕትሙ ዉስጥ ያሉት ምልከታዎች በምንም ዓይነት መልኩ የተባበሩት መንግስታት የአካባቢ ፕሮግራምን ሃሳብ፤ ድርጅቱ ከሌሎች ሀገሮች ጋር ያለዉን ህጋዊ ግንኙነት ወይም የሃገራትን ህጋዊነት፤ ድንበር ወይም ከተማ ወይም የሚመለከተዉን ባለስልታን አያንጸባርቁም።

የተባበሩት መንግስታት የአካባቢ ፕሮግራም, 2017. ደን በኢትዮጵያ ሀገራዊ ገቢ ላይ ያለው አስተዋፅኦና ከ'ደን መጨፍጨፍና መመናመን ምክንያት የሚለቀቅ በካይ ጋዝ ቅነሳ' (REDD+) ጋር ያለው ተያያዥነት. የተባበሩት መንግስታት የአካባቢ ፕሮግራም፡ ናይሮቢ

## የፕሮጀክቱ አስተባባሪዎች

ተፈራ መንግስቱ ወልዴ፡- ብሔራዊ አስተባባሪ፤ የደን ዘርፍ ልማት አቅም ግንባታ ፕሮግራም፤ የተባበሩት መንግስታት የልማት ፕሮግራም/የአካባቢ፣ ደንና የአየር ንብረት ለውጥ ሚኒስቴር፣ ኢቮ ሙልደር፣ አማካሪ፣ በ'ደን መጨፍጨፍና መመናመን ምክንያት የሚለቀቅ በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮጀክት' (REDD+) ኢኮኖሚክስ፤ የተባበሩት መንግስታት የአካባቢ ፕሮግራም (UNEP)፤ አባቡ አናጊ፣ የብሔራዊ የአየር ንብረት ለውጥ ስፔሻሊስት፤ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ልማት ክፍል፣ የተባበሩት መንግስታት የልማት ፕሮግራም

## የፅሑፉ አዘጋጆች

ሮበርት ስሚዝ፤ ሚድሰመር አናሊቲክስ (ዋና ፀሐፊ)፣ ኬራን ማክዱጋል እና ጄሲካ ሜቱዛልስ፡- ሚድሰመር አናሊቲክስ (ረዳት ተመራማሪ)፣ ኮሪና ራቪሊየስ፤ ዋና የጂ አይ ኤስ ኦፊሰር፣ እና አርኖት ቫን ሶስበርገን፤ የፕሮግራም ኦፊሰር፣ UNEP-WCMC (ስፓሺያል አናሊሲስ)

## አርታኢዎች

ኢቮ መልደር፣ አማካሪ፣ በ'ደን መጨፍጨፍና መመናመን ምክንያት የሚለቀቅ በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮጀክት' (REDD+) ኢኮኖሚክስ የተባበሩት መንግስታት የአካባቢ ፕሮግራም (UNEP)፣ ጃሚ ዌብ፣ በ'ደን መጨፍጨፍና መመናመን ምክንያት የሚለቀቅ በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮጀክት' (REDD+) ስራ አመራር ኦፊሰር፤ የተባበሩት መንግስታት የአካባቢ ፕሮግራም(UNEP)

## ምስጋና

ከዚህ በታች ስማቸው የተዘረዘረው ሰዎች ትብብርና የኤክስፐርት/የባለሙያ ምሪት ባይገኝ ኖሮ ይህንን ሪፖርት ለማዘጋጀት የማይቻል ነበር፡-

በኢትዮጵያ የብሔራዊ አካውንቶች ስርዓት ላይ በአማካሪነት፡ - ልኡልሰገድ ደቻሳ፣ ዳይሬክተር የብሔራዊ አካውንቶች ዳይሬክቶሬት፤ የገ/ኢ/ል/ሚ፤ ፍትህአወቅ መታፈሪያ በየነ፣ የቴክኒክ ቡድን አስተባባሪ፤ የብሔራዊ የኢኮኖሚ አካውንቶች ዳይሬክቶሬት፣ የገ/ኢ/ል/ሚ

በደን ስነ-ምህዳር ውጤቶችና አገልግሎቶች መረጃ/የማማከር አገልግሎት፡- ተስፋዬ ይመር፣ የቡድን መሪ፣ ሰንኮፋ የማማከር አገልግሎት፤ ተክለሐይማኖት ንጋቱ፤ ዋና ስራ አስፈፃሚ ኦፊሰር፤ ብሔራዊ የጐማ ዛፍ ማቀናበሪያና ሽያጭ ድርጅት፤ ተስፋዬ አዋስ፤ የስነ-እፅዋት ባለሙያ፤ የኢትዮጵያ ብዝሀ-ሕይወት ኢንስቲቲዩት፤ ውብአለም ታደሰ፤ ዋና ዳይሬክተር፤ የኢትዮጵያ የአካባቢና የደን ምርምር ኢንስቲቲዩት፤ ታደሰ ወልደማርያም ጐሌ፤ ዳይሬክተር፤ የአካባቢና የጫካ ቡና ፎረም፤ አረጋ መኮንን፤ የብሔራዊ ፕሮጀክት አስተባባሪ፤ የተከለሉ አካባቢዎች ቀጣይነት ያለው ልማት ስርዓት በኢትዮጵያ፤ ገዛኸኝ አባተ፤ የሕዝብና የአለም ዓቀፍ ግንኙነቶች ዳይሬክተር፤ የኢትዮጵያ የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር፤ ጁሊያን ጐንዛሎ፤ የአለም ዓቀፍ የግምገማ ሪፖርትና ማረጋገጥ ስፔሻሊስት፤ በ'ደን መጨፍጨፍና መመናመን ምክንያት የሚለቀቅ በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮጀክት' (REDD+) ሴክሬታሪያት፤ የአካባቢ፣ ደንና አየር ንብረት ለውጥ ሚኒስቴር

የስፓሺያል ሞዴሊንግ እና ዋጋ ትመና ኤክስፐርት፡- ኮሪና ራቪሊየስ፤ ዋና የጂ አይ ኤስ ኦፊሰር፣ UNEP-WCMC፤ አርኖት ቫን ሶስበርገን፣ የፕሮግራም ኦፊሰር፤ UNEP-WCMC፤ ጀምስ ቮዝ፤ ዋና ኢኮኖሚስት፤ UNEP-WCMC፤ ሌራ ማይልስ፤ የአየር ንብረት ለውጥና የብዝሀ-ሕይወት ፕሮግራም፣ UNEP-WCMC

ድጋፍ፡- ይተብቱ ሞገስ አበበ፤ በ'ደን መጨፍጨፍና መመናመን ምክንያት የሚለቀቅ በካይ ጋዝ ቅነሳ' (REDD+) ሴክሬታሪያት አስተባባሪ፤የአካባቢ፣ ደንና አየር ንብረት ለውጥ ሚኒስቴር፤ፋቢየን ሞንቴሊስ፤ ከፍተኛ የቴክኒክ አማካሪ፤ የተባበሩት መንግስታት የአካባቢ ፕሮግራም (UNEP)፤ ጃሚ ዌብ፤ የፕሮግራም ስራ አመራር ኦፊሰር፤ የተባበሩት መንግስታት የአካባቢ ፕሮግራም (UNEP)፤ ዩንሂ ኪም፤ አውትሪቾ ስፔሻሊስት፤ የተባበሩት መንግስታት የአካባቢ ፕሮግራም (UNEP) በአፍሪካ ሕብረት ላይዘን ኦፊስ፤ UNECA እና ኢትዮጵያ

አጠቃላይ የስራ አመራር፡- ክቡር አቶ በለጠ ታፈረ፣ ሚኒሰትር፣ አካባቢና ደን እንድሁም ክቡር አቶ ከበደ ይማም፣ ሰቴት ሚኒስትር፣ አካባቢና ደን ሚኒስቴር

# ዋና ዋና ግኝቶች

- **ደን በኢትዮጵያ ሀገር-አቀፍ ገቢ ውስጥ ያለው አስተዋፅኦ፡-** ይህ ሪፖርት በደረሰበት ማጠቃለያ መሠረት በ2012-13[1] እኤአ የኢትዮጵያ ደን በጥሬ ገንዘብ እና በዓይነት 111.2 ቢሊየን የኢትዮጵያ ብር (16.7 ቢሊየን የአሜሪካ ዶላር) ገደማ ወይም ከአጠቃላይ የሀገር ውስጥ ምርት 12.86% የሆነ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታን አስገኝቷል፡ ፡ ይህ አሃዝ ከዚህ ቀደም ከሚታሰበው አንፃር ሲታይ ከፍተኛ መጠን ያለው ነው፡፡ ከዚህ ውስጥ 6.09% የአጠቃላይ የሀገር ውስጥ ምርት ድርሻን የሚይዘው የደን ኢንዱስትሪው ነው፡፡ የደን ስነ-ምህዳር ለሌሎች ዘርፎች በተለይም ለግብርናው ዘርፍ የሚያበረክተው አስተዋፅኦ የአጠቃላይ የሀገር ውስጥ ምርት ዋጋን 6.77% የሚይዝ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ 2.4 ቢሊየን የኢትዮጲያ ብር ኢትዮጵያዊያን ለደን ጥበቃ ባላቸው ፍቃደኝነት መሠረት ገበያ-ነክ ላልሆኑ ጥቅሞች ውሏል፡፡[2]
- **ጠቃሚ የደን ውጤቶችና አገልግሎቶች፡-** ከሸያጭ የሚገኘው ከፍተኛ ገቢ ከማገዶ እንጨት (ከሰልን ጨምሮ) ፍሰትና ከደን ከሚገኙ የከብቶች መኖ ጋር ተያያዥነት ያለው ነው፡፡ ከላይ የተጠቀሱት በጋራ 62% (69.0 ቢሊየን የኢት. ብር ወይም 10.3 ቢሊየን የአሜ. ዶላር) ከደን የሚገኝ ጥቅምን ያስገኛሉ፡፡ በኢትዮጵያ ውስጥ በሰፊው አገልግሎት ላይ የሚውሉ በመሆኑ ምክንያት የማገዶ እንጨትና የከብቶች መኖ ከፍተኛ ጠቀሜታ አላቸው፡፡ መኖን በተመለከተ ግብርና ለሀገሪቱ ምጣኔ ሀብት ከፍተኛ አስፈላጊነት ያለው መሆኑ ሌላኛው ምክንያት ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የአጣና/roundwood/ አቅርቦት (11.4% የአገልግሎት ጥቅም)፣ የጫካ ቡና ምርት (10.8%)፣ የሰብል መሬቶች መሸርሸርን መከላከል (6%)፣ በጫካ ነፍሳት አማካኝነት የሰብሎች መዳቀል (4.5%)፣ የጫካ ማር/የሰም ምርት (1.5%) እና መድኃኒትነት ያላቸው የዱር ዕፅዋት (1.1%) ከደን ለሚገኝ ገቢ ጠቃሚ ምንጮች ሆነው ተገኝተዋል፡፡
- **በሀገር-አቀፍ ኢኮኖሚ ውስጥ ደን ያለው ኢኮኖሚያዊ አስተዋፅኦ ዝቅተኛ ግምት የተሰጠው ስለመሆኑ፡-** በዚህ ሪፖርት ላይ ጥቅም ላይ የዋሉት ሁሉም የዋጋ ተመና ዘዴዎች ከብሔራዊ ሒሳቦች ስርዓት ጋር ተጣጣሚነት ያላቸው ሲሆን፤ ይህ ማለት የተቀመጠው የግምት ውጤት ከመርህ አንፃር በጂዲፒ ውስጥ የሚንፀባረቅ ነው ማለት ነው፡፡ ግኝቶቹ እንደሚጠቁሙት ወቅታዊው የአጠቃላይ የሀገር ውስጥ ምርት ግምቶች የደኑ ዘርፍ ለብሔራዊ ገቢ የሚያበረክተውን አስተዋፅኦ እስከ 42% ዝቀ አድርገው ግምት የሰጡት ሲሆን፤ ይፋዊ ስታቲስቲክሶች እንደሚያሳዩት ዘርፉ ያበረከተው አስተዋፅኦ 3.8% ስለመሆኑ ነው (የፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር/ MOFED/, 2015 እኤአ)፤ ነገር ግን በዚህ ጥናት የዘርፉ አስተዋጽኦ 6.09% እንደሆነ ይገመታል፡፡ በተጨማሪ ከላይ እንደተገለጸው ከሌሎች ዘርፎች በተለይም ከግብርናው ዘርፍ የሚገኙ ደንን መሰረት ያደረጉ የገንዘብና የዓይነት ገቢዎች መጠን 6.77% የአጠቃላይ የሀገር ውስጥ ምርት እንደሆነ ይገመታል፡፡
- **የፖሊሲ አወጣጥ አማራጮች፡-** እነዚህ ግኝቶች ከሌሎች ጥቅሞች ባሻገር የፋይናንስና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር (በፊት የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የነበረው)፣ ማዕከላዊ የስታቲስቲክስ ኤጀንሲ እና የግብርና ሚኒስቴር የኢትዮጵያ ደን ለኢኮኖሚው ምን ያህል አስተዋፅኦ እያበረከተ እንደሆነ በተሻለ ሁኔታ እንዲገነዘቡ በማድረግ በ'ደን መጨፍጨፍና መመናመን ምክንያት የሚለቀቀ በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮጀክት' (REDD+ Secretariat) በኢትዮጵያ ውስጥ ያለበትን ሂደት እንዲጠናከር ያደርጋሉ፡ ፡ ይህ ሁኔታ ደግሞ የበለጠ ትክክለኛነት ያለው ደን በአጠቃላይ የሀገር ውስጥ ምርት የሚያበረክተውን ጥቅሞች በማስቀመጥና የሳተላይት የደን አካውንቶችን በማዘጋጀት የኢትዮጵያ የብሔራዊ አካውንቶች ስርዓትን (ESNA) ለማሻሻል መሰረት ይጥላል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ውጤቶቹና አስተያየቶቹ በ'ደን መጨፍጨፍና መመናመን ምክንያት የሚለቀቀ በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮጀክት' (REDD+ Secretariat) ብሔራዊ ስትራቴጂ ውስጥና በበለጠ ደግሞ በሁለተኛው የኢትዮጵያ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ (GTP 2) ሊካተቱ ይችላሉ፡፡

## የፕሮጀክቱ ዓላማዎች

በ2014 እአአ የኢትዮጵያ መንግስት የተባበሩት መንግስታት - በ'ደን መጨፍጨፍና መመናመን ምክንያት የሚለቀቀ በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮጀክት' (UN-REDD) የሀገሪቷን የደን ስነ-ምህዳር ከብሔራዊ በ'ደን መጨፍጨፍና መመናመን ምክንያት የሚለቀቀ በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮጀክት' (REDD+ project) ሂደት አንፃር በብሔራዊ ገቢ ላይ ያለውን አስተዋፅኦ ለመገምገም ድጋፍ እንዲያደርግለት ጠይቋል፡፡ የፕሮጀክቱ ዋነኛ ዓላማ ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ነጥቦች ላይ ጥናት በማካሄድ የኢትዮጵያ ደን በብሔራዊ ገቢ[3] (ጂዲፒ) ላይ ያለውን አስተዋፅኦ ማወቅ ነው፡፡

- **የደን ዘርፉ ተጨማሪ እሴት፡-** በኢትዮጵያ የብሔራዊ አካውንቶች ስርዓት ውስጥ የደን ስነ-ምህዳር ውጤቶችና አገልግሎቶች በየዓመቱ ከደን ኢንዱስትሪው ለጂዲፒ የሚደረግ አስተዋፅኦ፡፡
- **የደን ስርዓተ-ምህዳር ለሌሎች ዘርፎች የሚያበረክተው አስተዋፅኦ፡-** የደን ስርዓተ-ምህዳር ውጤቶችና አገልግሎቶች ምርት በESNA ውስጥ ለሚገኙ ለሌሎች ኢንዱስትሪዎች የሚያበረክተው ዓመታዊ አስተዋፅኦ (ለምሳሌ፡- በደን ላይ የተመሰረተ የነፍሳት ርክበ-ብናኝ ለግብርናው ኢንዱስትሪ የሚጨምረው ተጨማሪ እሴት ወይም የተከለሉ ቦታዎች ለቱሪዝም ኢንዱስትሪ የሚኖረው አስተዋፅኦ)፡፡
- **ገበያ-ነክ ያልሆኑ ጥቅሞች፡-** የደን ስርዓተ-ምህዳር በኢትዮጵያ ውስጥ ላለው ገበያ-ነክ ያልሆነ ገቢ የሚያበረክተው ዓመታዊ አስተዋፅኦ (በንድፍ ሐሳብ ደረጃ ይህ ከብሔራዊ አካውንቲንግ ዓላማ ውጭ በመሆኑ በጂዲፒ ውስጥ ያልተካተተ)

---

1. የዚህ ጥናት ዋና ዋና ግኝቶች ለኢትዮጲያ 2012-13 እአአ በጀት ዓመት እኤአ ሪፖርት ተደርገዋል፡፡ ምክንያቱም ይህ ዓመት የደን ስርዓተ-ምህዳር ውጤቶችና አገልግሎቶችን የተሻለ ግምት ለማስቀመጥ አመቺ ነበር፡፡
2. ገበያ-ነክ ያልሆኑ ገቢዎች በመርህ ደረጃ ከጂዲፒ ግምቶች ጋር አይጣጣሙም፡፡ በመሆኑም በዚህ ጥናት ውስጥ ለብቻ ተለይተው ሪፖርት ተደርገዋል፡፡
3. ገበያ-ነክ ያልሆኑ ገቢዎች በመርህ ደረጃ ከጂዲፒ ግምቶች ጋር አይጣጣሙም፡፡ በመሆኑም በዚህ ጥናት ውስጥ ለብቻ ተለይተው ሪፖርት ተደርገዋል፡፡

የደን ስርዓተ-ምህዳር ለብሔራዊ ገቢ የሚያደርገው አስተዋፅኦ በኢትዮጵያ ውስጥ ለሚደረገው የደን ጥበቃ ስራ ወሳኝ ነው፡ ፡ ከዚህ ጥናት በፊት ከደን ከሚገኙ ውጤቶችና ምርቶች የሚገኘው ገቢን በተመለከተ ሙሉ ግምገማ ወይም ግምት በደን ዘርፉ ወይም በሌሎች ዘርፎች አልተከናወነም፡ ፡ ብቸኛውና ይፋዊው የነበረው አህዛዊ ግምት የESNA (የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር 2015 እአአ) ሲሆን በዚህ መሰረት የደን ኢንዱስትሪ ለጂዲፒ የሚያደርገው አስተዋፅኦ እአአ በ2012-13 በተጠናው ጥናት 3.8% ተገምቷል። ደን ለገበያና ገበያ-ነክ ላልሆኑ ገቢዎች የሚያበረክተውን አስተዋፅኦ ሙሉ በሙሉ በመገምገም የበለጠ የተሟላ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታውን የሚያመላክት ምስል ማግኘት ይቻላል።

## ነባራዊ ሁኔታ

ከ90 ሚሊዮን በላይ ሕዝብ ያላት ኢትዮጵያ በምስራቅ አፍሪካ ከፍተኛው የሕዝብ ቁጥር ያላትና በመላው አፍሪካ ከናይጄሪያ ቀጥሎ ሁለተኛዋ ከፍተኛ የሕዝብ ቁጥር የሚኖርባት ሀገር ነች። ዓመታዊ የሕዝብ ቁጥር እድገት ከ2% በላይ ሲሆን ይህ ማለት በ2030 እአአ የኢትዮጵያ የሕዝብ ብዛት ወደ 120 ሚሊዮን ከፍ ሊል ይችላል ማለት ነው። አብዛኛው ሕዝብ የሚኖረው በገጠራማ አካባቢዎች ነው። በከተማ ውስጥ የሚኖሩት ኢትዮጵያዊያን 17% ብቻ ሲሆኑ፤ ከዚህ ውስጥ ግማሽ ያህሉ ሕዝብ የሚኖረው በመዲናችን አዲስ አበባ ነው።

ኢትዮጵያ ተፈጥሯዊ ልዩነቶች ያሉባት ምድር ነች። የቆዳ ሽፋኗ ከ1.1 ኪ.ሜ2 በላይ ሲሆን፤ የተለያዩ የአየር ንብረት ቀጠናዎችና የአፈር ሁኔታዎችን ይይዛል። በ2013 እአአ በተዘጋጀው የኢትዮጵያ የመሬት ሽፋን ካርታ መሠረት ደን ከአጠቃላይ የሀገሪቱ መሬት ውስጥ 162,000 ኪ/ሜ2 የሚሸፍን ሲሆን በዛፍ እና በቁጥቋጦ የተሸፈነ መሬት 492,000 ኪ/ሜ2 ይሸፍናል (የኢትዮጵያ ካርታ ስራዎች ኤጀንሲ 2013 እአአ) (ከታች ያለውን ምስል 1 ይመልከቱ)።

ከካርቦን ነፃ የሆነ የዕድገት መንገድን በመከተል በ2025 እአአ ሀገሪቱ መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገራት ተርታ እንድትመደብ ለማድረግ ዓላማ በመያዝ በ2011 እአአ የኢትዮጵያ መንግስት ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ ስትራቴጂን ይፋ አድርጓል። ከ'ደን መጨፍጨፍና መመናመን ምክንያት የሚለቀቅ በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮጀክት' (REDD+) ተግባራዊነት[4] የዚህ ስትራቴጂ አንደኛው ምሰሶ ነው (የኢትዮጲያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ 2011 እአአ)።

በስትራቴጂው መሠረት፤ በ2010 እአአ የኢትዮጵያ የበካይ ጋዝ ልቀት ወደ 150 ሜጋ ቶን CO2 የሚጠጋ ነበር። በተለመደው የልማት ስትራቴጂ ይህ ልቀት በ2030 እአአ ከእጥፍ በላይ 400 ሜጋ ቶን CO2 ይሆናል ተብሎ ይጠበቃል። ከ'ደን መጨፍጨፍና መመናመን ምክንያት የሚለቀቅ በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮጀክት' (REDD+) የበካይ ጋዝ ልቀቱን አሁን ባለበት ደረጃ በሚጠጋ መጠን ከመቆጣጠሩ በተጨማሪ ሀገሪቱ የልማት ግቦቿን እንድታሳካ ጉልህ ድጋፍ ያደርጋል።


የሰው ልጅ በደኖች ላይ የሚያደርሰው አሉታዊ ተጽእኖ ለኢትዮጵያ የበካይ ጋዝ ልቀት ጉልህ ሚና አላቸው። በ2010 እአአ ከደን ጋር ተያያዥ የሆኑ ልቀቶች ወደ 55 ሜጋ ቶን CO2 አካባቢ የነበረ ሲሆን ለዚህም ምክንያቶቹ ለእርሻ መሬት ደኖችን መመንጠር (ከደን ጋር ተያያዥ የሆኑ ልቀቶች ሁሉ 50% ያህል የሚሸፍን)፣ ለማገዶ እንጨት ፍጆታ ደኖችን ማራቆት (46%) እንዲሁም መደበኛና መደበኛ ያልሆኑ የደን እንጨት ቆረጣ ስራዎች (4%) ናቸው። እነዚህ ዋነኛና ቀጥተኛ የደን መራቆትና መመናመን ምክንያት ከሆኑት መካከል ተጠቃሽ ናቸው።

ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ ስትራቴጂ እንደሚያስገነዝበው ሀገሪቱ የልማት ግቦቿን ለማሳካት እንድትችል የደን ምንጠራና መመናመን መገታት ይኖርበታል፡ ፡ በኢትዮጵያ ውስጥ ከ80% በላይ የሚሆኑት አባወራዎች የሀይል አቅርቦት የሚያገኙት ከማገዶ እንጨት ሲሆን በተለይም የማገዶ እንጨት በገጠር አካባቢዎች ከፍተኛ አስፈላጊነት አለው። ከማገዶ እንጨት በተጨማሪ ደን ሌሎች የጣውላ ምርቶችን እንዲሁም የከብቶች መኖ፣ ቡና እና ማርን ጨምሮ ሌላ እንጨት-ነክ ያልሆኑ ጠቃሚ ምርቶችን ይሰጣል። ከዚህ በተጨማሪ ደን የካርቦን ልቀትን መቀነስ፣ የሰብሎች መዳቀል፣ የእርሻ መሬቶችን ለምነት መጠበቅ፣ ወደ ወንዞችና ጅረቶች የሚለቀቅ ውሃን መቆጣጠርን ጨምሮ ወሳኝ የሆኑ የስርዓተ-ምህዳር አገልግሎቶችን ይሰጣል።

ደን ኢኮኖሚያዊና ስነ-ምህዳራዊ ጠቀሜታ ያለው ቢሆንም በአሁኑ ወቅት የኢትዮጵያ ደን አደጋ ላይ ሲሆን በሌላ መልኩ በቁጥር እየጨመረ የመጣው የሀገሪቱ ሕዝብ ተጨማሪ የማገዶ እንጨትና ምግብ ያስፈልገዋል። እነዚህ ፍላጎቶች በተራቸው የደን መጨፍጨፍና መመናመንን በጉልህ ሁኔታ ያፋጥናሉ። ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ ስትራቴጂ ላይ የተቀመጡ ዕቅዶች እንደሚያሳዩት ሀገሪቱ የልማት ጉዳናውን አቀጣጫ ባትቀይር ኖሮ ከ2010 እአአ እስከ 2030 እአአ ባለው ጊዜ ውስጥ 90 ሺህ ኪ/ሜ2 (ከአጠቃላይ የደን ሽፋን 56%ቱ) ሊራቆት ይችል ነበር። በተመሳሳይ ጊዜ ውስጥም ዓመታዊ የማገዶ እንጨት ፍጆታ በ65% ከፍ ሊል ይችላል።

4. REDD (ከ'ደን መጨፍጨፍና መመናመን ምክንያት የሚለቀቅ በካይ ጋዝ ቅነሳ ፕሮጀክት') በ2008 እአአ ብቅ ያለ ዘርፈ-ብዙ የአሰራር ዘዴ ሲሆን ከ'ደን መጨፍጨፍና መመናመን ምክንያት የሚለቀቅ በካይ ጋዝን በመቀነስ ሂደት በማደግ ላይ ላሉ ሀገራት የሚደረግ የፋይናንስ ድጋፍ ነው። REDD+ የተሻሻለው የዚሁ የአሰራር ዘዴ ሲሆን ቀጣይነት ያለው የደን እንክብካቤ፣ በደን ውስጥ የሚኖረውን የካርቦን መጠን መጨመርና መጠበቅ፣ ወዘተ ያካትታል። እአአ በ2013 የዋርሳው ፍሬምወርክ በሚባል ስር የዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ በዝርዝር የREDD+ ጉዳዮች ላይ ስምምነት ላይ ደርሰዋል። የREDD+ ተግባራት የአፈፃፀም ቅደም ተከተል እና ውጤትን መሰረት ያደረገ የክፍያ ስርዓት በአሁኑ ሰዓት ስራ ላይ ውሏል።

**ምስል 1፡-** የኢትዮጵያ የደን ሽፋን




እነዚህን አሉታዊ ውጤቶች ለማስወገድ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ ስትራቴጂ የበለጠ ቀጣይነት ያለው የደንና የእርሻ ስራ ልማዶችን ለማጠናከር ለሚከተሉት ጉዳዮች ቅድሚያ ይሰጣል፡face-

- የከብቶችን ፍግና የዕፅዋት ብስባሽ በተሻሻለ ሁኔታ ጥቅም ላይ በማዋል የግብርና ስራውን ማጠናከርና ለግብርና ተብሎ ከደኖች ላይ የሚወሰደውን ተጨማሪ መሬት መቀነስ፡፡
- የመስኖ አጠቃቀምን በማሻሻል የግብርና ስራዎችን በተራቆቱ መሬቶች ላይ ማስፋፋት፡፡
- የበለጠ ውጤታማ የሆኑ የማገዶ ቆጣቢ ወይም አማራጭ የሀይል ምድጃዎችን በማሰራጨት የማገዶ እንጨት ፍላጎትን መቀነስ፡፡
- ደኖችን መልሶ በመትከል፣ የተመናመኑ ደኖችን ሽፋን በመጨመርና የተሻሻለ የደን እንክብካቤ ተግባራትን በማስፋፋት በደኖችና በዛፍ በተሸፈኑ መሬቶች ላይ የሚገኘውን የካርቦን ልቀት ቅነሳ መጨመር፡፡

## የጥናቱ ወሰንና የግምገማው ዘዴ

ከደን የሚገኝ ገቢ ግምት ጥናት በመላው ኢትዮጵያ ውስጥ የተከናወነ ነበር፡፡ ንዑስ ሀገር-አቀፍ ግምቶችን ለማጠናቀር የተደረገ ጥረት የለም፡፡ ትኩረት የተደረገው በሀገሪቱ ውስጥ ባሉ አጠቃላይ ደኖችና በሚሰጡት ጠቃሚ የስርዓተ-ምህዳር ውጤቶችና አገልግሎቶች ላይ ነው፡፡ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት የስነ-ምህዳር ውጤቶችና አገልግሎቶች ላይ ግምገማ ተደርጓል፡-

- የሚሰጡት ውጤቶችና ግልጋሎቶች
  - የጣውላ ምርቶች
  - የማገዶ እንጨት/ከሰል
- ከደን የሚገኙ እንጨት-ነክ ያልሆኑ ምርቶች
  - የከብቶች መኖ
  - ቡና
  - ማር
  - ሰም
  - ለመድሀኒትነት የሚያገለግሉ ዕፅዋት
  - እጣንና እና ሙጫ
  - ቅመማ ቅመም
  - ለቤት ጣሪያ መክደኛነት የሚያገለግል ሳር
  - ከዱር አራዊት የሚገኝ ስጋ
  - የሚበሉ የዱር ዕፅዋት
  - ዝባድ
  - የሀር ትል ኩኩን
  - ማቅለሚያዎችና የቆዳ ማለስለሻዎች
- የቁጥጥር አገልግሎቶች
  - የካርቦን ልቀት ቅነሳ
  - ርክበ-ብናኝ
  - የውሃ ፍሰት ቁጥጥር
  - የአፈር መሸርሸር ቁጥጥር
  - የውሃ ማቆሪያ ደለል ቁጥጥር
- ባህላዊና የመዝናኛ አገልግሎቶች
  - ለቱሪዝም የተከለሉ ቦታዎች
  - ሕጋዊ አደን
  - ዋጋ ያልወጣላቸው ጠቀሜታዎች

ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው በጥናቱ ውስጥ የተለካው ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ዓመታዊ የደን ስርዓተ-ምህዳር ውጤቶችና አገልግሎቶች ያላቸው ገበያና ገበያ-ነክ ያልሆነ ገቢዎች ኢኮኖሚያዊ ፍሰት ነው። እስካሁን ባለው የኢትዮጵያ ደኖች በተፈጥሮአዊ ንብረትነት ያላቸውን የስቶክ ዋጋ ለማስላት የተደረገ ጥረት የለም። በሌላ መልኩ አሁን ያለውን ገቢ ፍሰት ቀጣይነት ወይም ስርጭት ለማወቅ የተደረገ ጥረትም አይታይም። በመሆኑም በአሁኑ ሰዓት ደንን መሰረት ያደረገ ገቢ ቀጣይነት በሌለውና ፍትሃዊ ባልሆነ የደን ስርዓተ-ምህዳር ውጤቶችና አገልግሎቶች የመጣ ሊሆን ይችላል።

ግምገማው በዋነኝነት የተካሄደው በዓለም አቀፍ የምርምር ቡድን አማካሪዎች አማካኝነት በጠረጴዛ ዙሪያ ነው። ከዚህ በፊት የነበሩት መረጃዎች ብቻ ጥቅም ላይ ውለዋል። ይሁን እንጂ የደን ስነ-ምህዳር ውጤቶችና አገልግሎቶች ለኢትዮጵያ የገጠር አባወራዎች ያላቸው ጠቀሜታ በተመለከተ ከፕሮጀክቱ ጋር ተጣጣሚ በሆነ መንገድ ከተደረገው ጥናት (ይመር 2016 እአአ) ይህ ግምገማ ተጠቅሟል። ጥናቱ በተጨማሪ በተባበሩት መንግስታት የአካባቢ ፕሮግራም (UNEP) የዓለም የጥበቃ ክትትል ማዕከል (UNEP-WCMC) የተደረገውን የደን ርክበብናኛ ሞዴሊንግና የአፈር መሸርሸር ቁጥጥር አገልግሎቶች ጥናት ተጠቅሟል።

ከዚህ በተጨማሪ በዚህ ግምገማ ወቅት ኢትዮጵያዊያን ባለሙያዎች ግምታዊ ትንታኔ በመስጠት አስተዋፅኦ አበርክተዋል። ኤክስፐርቶቹ ጥናቱ ላይ ተሳተፎ እንዲያደርጉ ያመቻቹት የአካባቢና ደን ሚኒስቴርና ከላይ ለተጠቀሰው የገጠር አባወራዎች ጥናት ኃላፊነትነቱን የወሰዱት የሀገር ውስጥ አማካሪ (ዶ/ር ተስፋዬ ይመር) ናቸው። በጥናቱ ዘዴዎች፣ መረጃዎችና ግምቶች ዙሪያ የፕሮጄክቱን ወሰን ለማስቀመጥ በሚያዝያ 2015 እአአ በአዲስ አበባ በተዘጋጀው ወርክሾፕ ላይ ጠቃሚ ምክሮች ተገኝተዋል።

በዚህ ግምገማ ውስጥ ጥቅም ላይ የዋሉት ንድፈ-ሀሳቦችና የጥናት ዘዴዎች ከስርዓተ-ምህዳር ግምገማ የፅሑፍ አዘገጃጀትና የተባበሩት መንግስታት የብሔራዊ አካውንቶች ስርዓት (የአውሮፓ ኮሚሽን እና ሎሎች 2009 እአአ)፣ የአካባቢያዊ-ኢኮኖሚያዊ አካውንቲንግ ማዕከላዊ አውታር (የተባበሩት መንግስታት እና ሌሎች 2014a እአአ) እና ከአካባቢያዊ-ኢኮኖሚያዊ አካውንቲንግ-የሙከራ የስርዓተ-ምህዳር አካውንቶች (የተባበሩ መንግስትታት እና ሌሎች 2014b እአአ) ጋር ተጓጋጊ ናቸው።

በአጠቃላይ ጥናቱ የከፋ እክል ያላጋጠመው ሲሆን ከስርዓተ-ምህዳር ዋጋ ትመና የሚጠበቀው የትክክለኛነት ደረጃ ምክንያታዊ እስከሆነ ድረስ የጥናቱ ውጤቶች መነሻ ሆነው ሊያገለግሉ ይችላሉ።

## የጥናቱ ውጤቶች

በአጠቃላይ የጥናቱ ውጤቶች የኢትዮጵያ ደኖች ከዚህ ቀደም ከሚታሰበው በላቀ ደረጃ ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታዎች እንዳላቸው ያሳያል። እስካሁን ድረስ የነበረው ግንዛቤ በተላኩት የጂዲፒ መረጃዎች መሠረት ሲሆን ለደን የተሰጠው ድርሻ 4% ብቻ ነበር። በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር 2015 እአአ የተቀመጠው ትክክለኛው ድርሻ በ2012-13 እአአ የተሰጠው ግምት ሲሆን 3.8% ነበር። የበለጠ ሰፋ ያለው ጥናት አሃዙን ወደ 12.9% ያህል እንደሆነ የሚያመለክት ሲሆን ገበያ-ነክ ያልሆኑ ደንን በመጠበቅ የሚገኙ ጠቀሜታዎችን ግን ከግምት አላስገባም።

**ከደን የሚገኙ ገቢዎች ከደን ውጭ ላሉ ኢንዱስትሪዎች ጂዲፒ ያላቸው ድርሻ፦** ደኖች በብሔራዊ አካውንቶች ውስጥ ከደን ውጭ ለሆኑ እንዱስትሪዎች ገቢ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያበረክታሉ። በተለይም ደኖች ለግብርናው ኢንዱስትሪ የጂዲፒ አስተዋፅኦ ከፍተኛውን የገቢ ፍሰት የሚያበረክቱ ምንጮች ናቸው። ከብት አርቢ አርሶ አደሮች ለቤት እንስሳቶቻቸው ከደን መሬት ላይ የሚያገኙት መኖ በዚህ ረገድ ጠቃሚነቱ የጎላ ነው። የእንስሳት መኖ ለከብት እርባታ ብቸኛውና ዋነኛው መካከለኛ ግብዓት በመሆኑና በአብዛኛው የኢትዮጲያ አርሶ አደር በነፃ የሚገኝ በመሆኑ በእንስሳት እርባታው ኢንዱስትሪ የሚጨመረው እሴት ደንን መሰረት ያደረገ መኖ ባለመኖሩ ምክንያት ከሚኖረው የላቀ ነው። ከደኖች የሚገኝ የመኖ[5] የግብአት ጭማሪ በ2012-13 እአአ (29.9 ቢሊዮን የኢት. ብር ወይም 4.5 ቢሊዮን የአሜ. ዶላር) እንደሆነ የሚገመት ሲሆን ይህ ደግሞ የኢትዮጵያ የፋይናንስና የኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር (MOFED 2015 እአአ) ባወጣው ሪፖርት መሠረት የግብርናውን ዘርፍ ከብት እርባታ የእሴት ጭማሪ 36% ያህል ነው።

- **ሌሎች በዚህ ጥናት መሠረት ከደን ውጪ ለሆኑ ኢንዱስትሪዎች የሚያበረክተው ጠቃሚ የገቢ ፍሰት የሚከተሉት ናቸው፦**
    - ደን የአፈር መሸርሸርን በመከላከል የሚጨምረው እሴት (6.6 ቢሊዮን የኢት. ብር ወይም 996 ሚሊዮን የአሜ. ዶላር፤ ከሰብል ልማት ጋር የተያያዘ)
    - ለደን ርክበ-ብናኝ አገልግሎቶች ያለው ተጨማሪ እሴት (5 ቢሊዮን የኢት. ብር ወይም 752 ሚሊዮን የአሜ. ዶላር፤ ከሰብል ልማት ጋር የተያያዘ)
    - የተከለሉ የቱሪዝም ቦታዎች (850 ሚሊዮን የኢት. ብር ወይም 127 ሚሊዮን የአሜ. ዶላር፤ ከሆቴሎች፣ ሬስቶራንቶች፣ የጉዞ እና የመገናኛ እንዲሁም የሕዝብ አስተዳደር መ/ቤቶች ጋር የተያያዘ)
- **ከደን የሚገኙ ለጥቅል ሀገራዊ ምርት የሚያበረክቱት ጥቅሞች የተሰጣቸው ዝቅተኛ ግምት፦** ከደን የሚገኙ ገቢዎች አብዛኞቹ ለፍጆታ የሚውል በዓይነት የሚገኝ የደን ውጤቶችና አገልግሎቶች ጋር ይያያዛሉ። ለምሳሌ ያህል አብዛኞቹ አባወራዎች ከገበያ ከመግዛት ይልቅ እራሳቸው የማገዶ እንጨት ስለሚለቅሙ ከፍተኛ መጠን ያለው ከማገዶ እንጨት ምርት የሚገኘው እሴት ጭማሪ በዓይነት ከሚገኝ ጥቅም ጋር ይያያዛል። የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር እንዳስቀመጠው ግምት ከሆነ በአሁኑ ወቅት ካለው 39.1 ቢሊዮን የኢት. ብር (5.9 ቢሊዮን የአሜ. ዶላር) ጋር ሲነፃፀር በ2012-13 እአአ በማገዶ እንጨት የተጨመረው 25.5 ቢሊዮን የኢት. ብር (3.82 ቢሊዮን የአሜ. ዶላር) ነው። አብዛኛው ልዩነት የመጣው በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ግምት ውስጥ ለፍጆታ የሚውለው የማገዶ እንጨት የዓይነት ገቢ ባለመካተቱ ነው።

    በሌላ መልኩ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የደን ገቢ ግምቱን ያሳነሰበት ምክንያት ከአይታ ውጪ በሆነው ኢኮኖሚ ለምርት የሚወጣውን ግምት ዝቅ በማድረጉ ነው (ለምሳሌ ህገወጥ የዛፍ ቆረጣ). ይህ በተለይም ለአጠና (Roundwood) ምርት እሴት ጭማሪ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በ2012-13 እአአ 4.1 ቢሊየን የኢት. ብር ወይም 615 ሚሊየን የአሜ. ዶላር ከአሁኑ አሃዝ 12.7 ቢሊየን የኢት. ብር (1.9 ቢሊየን የአሜ. ዶላር) ጋር ሲነፃፀር

5. የከብት አርቢ አርሶ አደሮች ለሰብል አምራች አርሶ አደሮች ለእንስሳት መኖ ዋጋ መክፈል ቢኖርባቸው መኖ ለከብት እርባታ እንደ ማዕከላዊ ግብዓት ሆኖ ወጪው በከብት እርባታ ላይ ከተጨመረ እሴት የሚቀነስ ይሆናል። በሰብል ልማት የሚጨመረው እሴት በዚህ ረገድ ከፍተኛ ይሆናል።

በጣም ያነሰ መሆኑ ነው። ከፍተኛ ግምት ያለው ነገር ግን የማይለካው ልዩነት የመጣው ህገወጥ የሆነው ምርት ግምት ውስጥ በመግባቱ ነው (ቀሪው ለአይነት የአጠና አባወራ ገቢ ዝቅተኛ ግምት የተሰጠ ነው)።

- **በጥቅል ሀገራዊ ምርት ውስጥ ያሉ ክፍተቶች፡**
  - በአንዳንድ ጉዳዮች ከደን ውጤቶችና አገልግሎቶች ጋር ተያያዥነት ያላቸው የገቢ ፍሰቶች በዚህ ወቅት እንደተለካው በሁሉም ጂዲፒዎች ውስጥ አልተካተቱም፡ ፡ ይሁን እንጂ ከነዚህ የትኞቹም ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያላቸው አይደሉም።


ከታች በተቀመጠው ምስል 2 እአአ በ2012-13 በተጠናው ጥናት ደን ለተለያዩ ገቢዎች የሚያበረክተው አስተዋጽኦ ተጠቃሏል። በስተግራ በኩል ያለው ሰማያዊ ባር/ሰንጠረዥ ደን ለብሔራዊ ገቢ የሚያበረከተውን አስተዋፅኦ ግምት ሲሆን ይህም በተለይ ከደን ኢንዱስትሪ ጋር የተያያዘና 6.09% የጂዲፒ ልኬት ያህል (ማለትም 52.8 ቢሊዮን የኢት. ብር ወይም 7.9 ቢሊዮን የአሜ. ዶላር) ማለት ነው። ከዚህ ውስጥ 27%ቱ ለደኑ ዘርፍ አምራቾች የተገኘ የገንዘብ ገቢ ግምት (የማገዶ እንጨት የመሳሰሉ የደን ምርቶችን የሚያመርቱ አባወራዎችን ጨምሮ) ነው። ቀሪው 73% የራሳቸውን የደን ውጤቶች የሚያመርቱና የሚጠቀሙ አባወራዎች በዓይነት ያገኙት ገቢ ነው።

ነጠብጣብ ያለበት በግራ በኩል የሚገኘው ባር/ሰንጠረዥ እዚህ ላይ ለማነፃፀሪያነት የቀረበውን የደን ዘርፍ አጠቃላይ የሀገር ውስጥ ምርት ላይ ያለውን 3.8% (የኢት. ብር 30.4 ቢሊየን ወይም 4.6 ቢሊየን የአሜ. ዶላር) የተጨማሪ እሴት አህዝ የሚያሳይ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር (2015 እአአ) ይፋዊ መግለጫ ሲሆን እዚህ የቀረበው ለንጽጽር ያህል ብቻ ነው። እዚህ ላይ ለማየት እንደሚቻለው በዚህ ጥናት ውስጥ የተደረጉ ግምገማዎች የሚያሳዩት ውጤት እንደሚጠቁሙት የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ግምት በጉልህ ሁኔታ ዝቅተኛ ነው። የዚህም ምክንያቶች ከዚህ በታች ተቀምጧል።

በመካከል የሚታየው ቀዩ ባር/ሰንጠረዥ ለESNA ከደን ውጪ ለሆኑ ኢንዱስትሪዎች የደን ስርዓተ-ምህዳር ውጤቶችና አገልግሎቶች ምርት ገቢ ጋር የተያያዘ ሲሆን ከእነዚህ አብላጫው ገቢ ከግብርናው ኢንዱስትሪ ጋር የተያያዘ ነው፡ ፡ ይህ ገቢ እዚህ ላይ በተደረገው ግምት መሠረት የጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት (GDP) ልኬት 6.77% ያህል ነው። ይህም በቀጥታ በጂዲፒ የተለካውን (ለአብነት ያህል የሰብል ልማት እሴት ጭማሪ ሆኖ የተለካውን የጫካ ቡና ዋጋ) እና በግልጽ በጂዲፒው የተለኩትን (ለአብነት ያህል ከደን የሚገኝ መኖ ልማት ዋጋና የሰብል ርከበ-ብናኝ አገልግሎቶች) ያጠቃልላል። በቀይ ባር/ሰንጠረዥ የተወከለው አብዛኛው ገቢ በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ይፋዊ ሪፖርት በቀጥታም ሆነ ቀጥተኛ ባልሆነ መንገድ የተካተተ ቢሆንም በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር መድሀኒትነት ያላቸው እጽዋትና የቤት ክዳን ሣር የተሰጠው ግምት በዚህ ጥናት መሰረት በጣም የወረደ መሆኑን ያመለክታል። በተጨማሪም የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በጫካ ቅመማ ቅመሞች፣ የዱር ስጋና የእጽዋት ምርት አማካኝነት የሚኖረውን እሴት ጭማሪ ምንም ዓይነት ግምት አልሰጠውም። የሰማያዊና የቀይ ባሮች/ሰንጠረዦች ድምር ከደን ስርዓተ-ምህዳር ውጤቶችና አገልግሎቶች የሚገኝ እሴት ጭማሪን ጠቅላላ ዋጋ ያመላክታል። በ2012-13 እአአ ይህ ምርት 111.2 ቢሊየን የኢት. ብር (16.7 የአሜ. ዶላር) ወይም 12.86% የጂዲፒ ልኬት ለሀገሪቱ ኢኮኖሚ አበርክቷል። በስተቀኝ የሚታየው አረንጓዴ ባር/ሰንጠረዥ ኢትዮጵያ የሀገሪቱን ደን ለመጠበቅ የሚፈፀም ክፍያ ለማድረግ ካላት ፈቃደኝነት ጋር ተያያዥነት ያላቸው ገበያ-ነክ ያልሆኑ የገቢ ጥቅሞችን የሚወክል ነው። አረንጓዴው ባር/ሰንጠረዥ ጽንሰ-ሀሳብ የተለየ በመሆኑ ከጂዲፒ ጋር በቀጥታ የሚነፃፀር አይደለም።

ምስል 2፡- ደን በብሔራዊ ኢኮኖሚ ላይ ያለው አስተዋፅኦ ማጠቃለያ እአአ 2012-13

**(አጠቃላይ የጥናቱ ውጤቶች ከታች በተቀመጠው ሰንጠረዥ 1 ላይ በአጭሩ ተጠቃሏል)።**



## ሰንጠረዥ 1፡- የውጤቶች ማጠቃለያ

| ውጤት/አገልግሎት | ለብሔራዊ ገቢ ያለው አስተዋፅኦ፤ 2012-13 እአአ | | | በኢትዮጵያ ብሔራዊ የአካውንት ስርዓት (SNA) ውስጥ በአሁኑ ወቅት የተለካ? | | | | የገቢ ዓይነት | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | አዎን | | የለም | | ቀጥታ | | | |
| | በሚሊዮን ኢት.ብር | በሚሊየን የአሜ. ዶላር | ድርሻ | በቀጥታ | በግልፅ ያልተቀመጠ | የመረጃ ክፍተት | ከወሰን ውጪ | የጥሬ ገንዘብ ድርሻ | የዓይነት ድርሻ | ቀጥተኛ ያልሆነ | ገበያ-ነክ ያልሆነ |
| 1. ውጤቶችና አገልግሎቶች አቅርቦት | | | | | | | | | | | |
| 1.1. ጣውላ-ነክ የደን ምርቶች | | | | | | | | | | | |
| 1.1.1. የማገዶ እንጨት | 39,078 | 5,858 | 4.52% | የደን ሣይንስ | | | | 18% | 82% | | |
| 1.1.2. አጠና | 12,700 | 1,904 | 1.47% | የደን ሣይንስ | | | | 53% | 47% | | |
| 1.1.3. ቀርከሃ/ሸምበቆ | 172 | 26 | 0.02% | የደን ሣይንስ | | | | 15% | 85% | | |
| ድምር፤ ጣውላ-ነክ የደን ምርቶች | 51,950 | 7,788 | 6.01% | | | | | | | | |
| 1.2. ጣውላ-ነክ ያልሆኑ የደን ምርቶች | | | | | | | | | | | |
| 1.2.1. የከብቶች መኖ | 29,900 | 4,482 | 3.46% | | የእንስሳት እርባታ | | | | | X | |
| 1.2.2. ቡና | 12,060 | 1,808 | 1.39% | የሰብል ልማት | | | | 99% | 1% | | |
| 1.2.3. ማር | 1,400 | 210 | 0.16% | የእንስሳት እርባታ | | | | 77% | 23% | | |
| 1.2.4. ሰም | 191 | 29 | 0.02% | የእንስሳት እርባታ | | | | 100% | 0% | | |
| 1.2.5. የመድሐኒት ዕፅዋት | 1,230 | 184 | 0.14% | የሰብል ልማት | | | | 44% | 56% | | |
| 1.2.6. እጣንና እና ሙጫ | 175 | 26 | 0.02% | የደን ሣይንስ | | | | 91% | 9% | | |
| 1.2.7. ቅመማ ቅመሞች | 310 | 46 | 0.04% | የሰብል ልማት | | | | 56% | 44% | | |
| 1.2.8. የቤት መከደኛ ሳር | 706 | 106 | 0.08% | የደን ሣይንስ | | | | 12% | 88% | | |
| 1.2.9. ከዱር እንስሳት የሚገኝ ስጋ | 461 | 69 | 0.05% | | | X | | 9% | 91% | | |
| 1.2.10. የሚበሉ የዱር እጽዋት | 257 | 39 | 0.03% | | | X | | 22% | 78% | | |
| 1.2.11. የጥርኝ ዝባድ | 0.4 | 0 | <0.01% | | | X | | 100% | 0% | | |
| 1.2.12. የሀር ትል ኩብኩባ/Coccon/ | 0.5 | 0 | <0.01% | የሰብል እርሻ | | | | መረጃ የሌለው | መረጃ የሌለው | | |
| 1.2.13. ማቅለሚያና የቆዳ ማለስለሻ ግብአቶች | መረጃ የሌለው | መረጃ የሌለው | መረጃ የሌለው | | | X | | መረጃ የሌለው | መረጃ የሌለው | | |

| | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ድምር፤ ጣውላ-ነክ ያልሆኑ የደን ምርቶች | 46,691 | 7,000 | 5.40% | | | | | | | | |
| ድምር፤ ውጤቶችና አገልግሎቶች አቅርቦት | 98,641 | 14,788 | 11.41% | | | | | | | | |
| 2. የቁጥጥር አገልግሎቶች | | | | | | | | | | | |
| 2.1. የካርቦን ልቀት ቅነሳ | 2.8 | 0 | ከ0.01% በታች | | | X | | 100% | 0% | | |
| 2.2. የዕፅዋት ርክበብናኝ (ፖሊኔሽን) | 5,013 | 752 | 0.58% | | የሰብል ልማት | | | | | X | |
| 2.3. የውሃ ፍሰት ቁጥጥር | መረጃ የሌለው | መረጃ የሌለው | መረጃ የሌለው | | የሰብል ልማት፣ ኤሌክትሪክና ውሃ | | | | | X | |
| 2.4. የአፈር መሸርሸር ቁጥጥር | 6,647 | 996 | 0.77% | | የሰብል ልማት | | | | | X | |
| 2.5. የውሃ አካላት ደለል ሙላት ቁጥጥር | መረጃ የሌለው | መረጃ የሌለው | መረጃ የሌለው | | የሰብል ልማት፣ ኤሌክትሪክና ውሃ | | | | | X | |
| ድምር፤ አገልግሎቶችን ሕጋዊ ማድረግ | 11,663 | 1,748 | 1.35% | | | | | | | | |
| 3. ባህላዊና የመዝናኛ አገልግሎቶች | | | | | | | | | | | |
| 3.1. የተጠበቁ/የተከለሉ የቱሪዝም በታዎች | 850 | 127 | 0.10% | | ሆቴል እና ሬስቶራንት፣ መጓጓዣና ኮሚኒኬሽን፣ የሕዝብ አስተዳደር | | | 100% | 0% | | |
| 3.2. የመዝናኛ ህጋዊ አደን | 19 | 3 | ከ0.01% በታች | | ሆቴል እና ሬስቶራንት፣ መጓጓዣና ኮሚኒኬሽን፣ የሕዝብ አስተዳደር | | | 100% | 0% | | |
| ድምር፤ የባህላዊና የመዝናኛ አገልግሎቶች | 869 | 130 | 0.10% | | | | | | | | |
| ጠቅላላ ድምር፤ ከደን የሚገኙ ውጤቶችና አገልግሎቶች | 111,173 | 16,666 | 12.86% | | | | | | | | |
| ውጤቶች* | 2,400 | 360 | መረጃ የሌለው | | | | X | | | | X |

*ጥቅም ላይ የማይውሉ የደን ውጤቶች ከሌሎች በሪፖርቱ ውስጥ ከተካተቱ እሴቶች ጋር ተያያዥነት የሌላቸው በመሆኑ በድምር ውስጥ አልተካተቱም። እነዚህ ጥቅሞች የተለኩት ደንበኞች ለመክፈል ባላቸው ዳሰሳ ሲሆን ይህም የደንበኞቹን ከፍጆታ ውጭ ያለ ምርት ከግምት ያስገባ ነው። ሌሎች ሁሉም እሴቶች የደንበኞችን ትርፍ ምርት ሳያካትት በገበያ ዋጋዎች ላይ ተመስርተው የተለኩ ናቸው።

የጥናት ውጤቶቹ የሚያሳዩት እዚህ ላይ ከተጠቀሱት ውጤቶቹና አገልግሎቶች በ2012-13 እአአ ከደን የሚገኙ ምርቶች አቅርቦት ለሀገር-አቀፍ ገቢ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አድርጓል። በዚህ መሰረት ከፍተኛ ጠቀሜታ ያለው የደን ምርት የማገዶ እንጨት (39.1 ቢሊየን የኢት. ብር ወይም 5.9 ቢሊዮን የአሜ. ዶላር፤ የጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት/GDP/ 4.5%) ሲሆን በጣም በቅርበት የሚከተለው ደግሞ የከብቶች መኖ (የኢት. ብር 29.9 ቢሊየን፤ 4.5 ቢሊየን የአሜ. ዶላር፤ የጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት/GDP/ 3.5%) ሆኖ ተገኝቷል። እነዚህ ምርቶች አስፈላጊ የሆኑበት ምክንያት በኢኮኖሚው ውስጥ በስፋት ጥቅም ላይ የሚውሉ በመሆኑ ሲሆን የከብቶች መኖን በተመለከተ ግብርና የሀገር ውስጥ ምርት/GDP/ ዋነኛ አካል በመሆኑም ጭምር ነው። ከመኖ ጋር ተያያዥነት ያለው ገቢ በአሁኑ ወቅት በቀጥታ በጠቅላላ የሀገር ውስጥ ገቢ ውስጥ ያልተለካ ቢሆንም የእንስሳት እርባታው ኢንዱስትሪ ተጨማሪ እሴት አካል ተደርጐ ግን በተዘዋዋሪ ተገልጿል። በሌላ በኩል ምንም እንኳን እዚህ ጥናት ላይ የሚታዩ ውጤቶች በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር በተዘጋጀው የጠቅላላ የሀገር ውስጥ ገቢ ቀጣይነት ባለው ሁኔታ የቤት ውስጥ ፍጆታን በተመለከተ ያልተሟላ ቆጠራ የተደረገ በመሆኑ በጉልህ ሁኔታ ዝቅተኛ ዋጋ የተሰጠው መሆኑን ቢጠቁሙም የማገዶ እንጨት ምርት ዋጋ የጠቅላላ የሀገር ውስጥ ገቢ አንድ ክፍል ተደርጐ ግን በቀጥታ ተሰልቷል። የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር ግምቶች በ2012-2013 እአአ የማገዶ እንጨት ምርት ተጨማሪ እሴት 25.5 ቢሊየን የኢት. ብር ወይም በዚህ ጥናት ላይ የተቀመጠውን ዋጋ 65% እንደነበር ያሳያሉ።

ከመኖና ከማገዶ እንጨት በመቀጠል የአጣና ምርት በገቢ ላይ ከፍተኛ (የኢት. ብር 12.7 ቢሊየን፤ 1.9 ቢሊየን የአሜ. ዶላር፤ የጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት/GDP/ 1.5%) አስተዋፅኦ አበርክቷል። አጣና አባወራዎች የሚያስፈልጋቸውን የግንባታ ማቴሪያል፣ መሣሪያዎችና ቁሳቁሶች ፍላጐት ለማሟላት ጥቅም ላይ ይውላል። ከዚህ በተጨማሪ ለጣውላና ለፕላይውድ የመሳሰሉት ማምረቻነት በጥሬ ዕቃነት ያገለግላል። አባወራዎች ለቤት ውስጥ ፍጆታ የሚጠቀሙበት በመሆኑ ምክንያት ወደ ግማሽ የሚጠጋው ከአጣና የሚገኝ ገቢ በዓይነት የተገኘ ነው። ከፍተኛ መጠን ያለው (ነገር ግን ሊለካ የማይችል) የዚህ ገቢ ድርሻ ሕገወጥ እና/ወይም ሪፖርት ያልተደረገ የአጣና ምርት የሚሰበሰብ ነው። ከፍተኛ መጠን ያለው (ነገር ግን ሊለካ የማይችል) የዚህ ገቢ ድርሻ ሕገወጥ እና/ ወይም ሪፖርት ያልተደረገ የአጣና ምርት የሚሰበሰብ ነው፡ ፡ የማገዶ እንጨትን በሚመለከት ያልተሟላ ሕገወጥ/ሪፖርት ያልተደረገ የአጣና ምርትና የቤት ውስጥ ፍጆታ አጠቃቀምን በሚመለከት ያልተሟላ ቆጠራ በመደረጉ ምክንያት የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር ያስቀመጠው የአጣና ተጨማሪ እሴት እጅግ ዝቅተኛ መሆኑን እዚህ ላይ የተቀመጡ ግኝቶች ይጠቁማሉ። የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር በ2012-13 እአአ ያስቀመጠው የአጣና ተጨማሪ እሴት የኢት. ብር 4.1 ቢሊዮን ወይም እዚህ ጥናት ላይ የተቀመጠው ዋጋ ግምት 31% ነው።

በቀጣይነት ከፍተኛ ጠቀሜታ ያለው ከደን የሚገኝ ምርት ቡና ሲሆን እዚህ ላይ በተቀመጠው ግምት መሰረት በ2012-13 እአአ የኢት. ብር 12 ቢሊዮን (1.8 ቢሊየን የአሜ. ዶላር፤ ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት/GDP 1.4%) ገቢ አስገኝቷል፡ ፡ ሁሉም ከቡና የተገኘ ገቢ ለሚያመርቱት አርሶ አደሮች የገባ የጥሬ ገንዘብ ገቢ ነው ለማለት የሚቻል ሲሆን በዓይነት ከተገኘ ገቢ ጋር ተያያዥነት ያለው ለቤት ውስጥ ፍጆታ የዋለው 1% ብቻ ነው። ምንም እንኳን የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር በተለይ ከደን ስለሚገኝ ቡና[6] ያዘጋጀው ግምት ባይኖርም ቡና በጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ውስጥ በቀጥታ ተሰልቷል። ከዚህ ይልቅ በጥቅሉ የቡናን ተጨማሪ እሴት (የጫካና የጫካ ያልሆነ) በመገመት የአነቃቂ ዕፅዋት ተጨማሪ እሴት ክፍል አድርጐ ሪፖርት አቅርቧል። ምንም እንኳን ከጫካ የሚገኝ ቡናን እሴት ጭማሪ ግምት ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር አሃዝ ጋር ለማነፃፀር ባይቻልም የዚህ ጥናት የትኞቹም ውጤቶች የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር የቡና እሴት ጭማሪ ግምት ከጫካ የሚገኝ ቡና ገቢን አለማካተቱን አያመላክቱም።

በዚህ ጥናት ውስጥ ከግንዛቤ ውስጥ ከገቡት ቀሪዎቹን የደን ምርቶች ማር/ሰም፣ የመድሐኒት ዕፅዋቶችና የባህላዊ ቤቶች የጣሪያ መክደኛ ሳር ከፍተኛ ጠቀሜታ አላቸው። እነዚህ ምርቶች በአጠቃላይ 3.5 ቢሊየን የኢት. ብር ወይም 530 ሚሊየን የአሜ. ዶላር፤ የሀገር ውስጥ ምርት/GDP 0.4% ያህል በገቢ እንደሆኑ ይገመታሉ። ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር ግምቶች ጋር ሲነፃፀር ከደን የሚገኝ የማር ምርት በአሁኑ ወቅት በተሰላው የጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ላይ ሙሉ በሙሉ ተካቷል። በሌላ በኩል የጣሪያ መክደኛ ሳር በወቅታዊው ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ገቢ ላይ ዝቅተኛ ግምት የተሰጠው ሲሆን መድሐኒትነት ያላቸው የዱር ዕፅዋት በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር ግምት ላይ በጉልህ ሁኔታ ዝቅተኛ ግምት ተሰጥቷቸዋል። እዚህ ላይ ልብ መባል የሚኖርበት እነዚህ ምርቶች በአጠቃላይ ለሀገሪቱ ገቢ ጉልህ አስተዋፅኦ የሌላቸው መሆኑንና ማንኛውም በኢትዮጲያ የብሔራዊ አካውንቶች ስርዓት/ESNA ግምቶች ላይ የሚኖሩ ስህተቶች በጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት/GDP ወይም በእድገቱ ምጣኔ ላይ ጉልህ የሆነ ለውጥ የማያስከትሉ መሆኑን ነው።

ቀሪዎቹ ከደን የሚገኙ ምርቶች (እጣንና ሙጫ፣ ከዱር እንስሳት የሚገኝ ስጋ፣ ለምግብነት የሚውሉ ዕፅዋቶች፣ የጥርኝ ዝባድ፣ የሀር ድር፣ ማቅለሚያና ማለስለሻ) በብሔራዊ ገቢ ላይ አነስተኛ አስተዋፅኦ እንዳላቸው ተገምቷል። በጥቅሉ በ2012-13 እአአ ወደ የኢት. ብር 1.2 ቢሊየን (174 ሚሊዮን የአሜ. ዶላር፤ የአጠቃላይ የሀገር ውስጥ ምርት/GDP 0.1% ያህል) የሚጠጋ ገቢ ማስገኘታቸው ታውቋል። እጣንና ሙጫን ሳያካትት (በአብዛኛው ለጥሬ ገንዘብ ገቢነት ለሽያጭ የሚውሉ በመሆናቸው) እነዚህ ምርቶች ለቤት ውስጥ ፍጆታ ጥቅም ላይ የሚውሉ በመሆናቸው ምክንያት በአብዛኛው በዓይነት የሚገኝ ገቢ የሚያስገኙ ናቸው።

6. ምንም እንኳን አብዛኛው በኢትዮጲያ ውስጥ የሚመረት ቡና በደን ላይ የተመሰረተ እንደሆነ ተደርጎ ቢወሰድም አንዳንድ የቡና እርሻዎች ከደን ውጪ ይገኛሉ።

ከደን ምርቶች በመቀጠል የደን የቁጥጥር ዋጋ ለብሔራዊ ገቢ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አለው። በእርሻ መሬት ላይ የሚደርስ የአፈር መሸርሸርን መከላከል (የኢት. ብር 6.6 ቢሊየን፤ 996 ሚሊየን የአሜ. ዶላር፤ የሀገር ውስጥ ምርት/GDP 0.8%) እና በደን ነፍሳት አማካኝነት ለግብርና ሰብሎች የሚደረግ ርክበ-ብናኝ (የኢት. ብር 5 ቢሊየን፤ 752 ሚሊዮን የአሜ. ዶላር፤ የሀገር ውስጥ ምርት/GDP 0.6%) ጉልህ አስተዋፅኦ አበርክተዋል። የደን የውሃ ፍሰት ቁጥጥር አገልግሎት ወይም የደለል ክምችት ቁጥጥር አሁን ባለው መረጃ መሠረት ሊለካ ወይም ሊገመት አልተቻለም። ምንም እንኳን በግብርናና በአገልግሎት ሰጪ ኢንዱስትሪዎች ውስጥ ያላቸው ተጨማሪ እሴት በተዘዋዋሪ የተካተተ ቢሆንም የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር በጂዲፒ ውስጥ በቀጥታ የእነዚህን አገልግሎቶች ዋጋ አልለካም ወይም አልገመተም።

ባህላዊና የመዝናኛ አገልግሎቶች በአጠቃላይ የሀገሪቱ ገቢ ላይ አነስተኛ አስተዋፅኦ እንደሚያበረክቱ ተገምቷል። የኢትዮጵያ የተከለሉ የቱሪዝም ቦታዎች በ2012-13 እአአ የኢት. ብር 850 ሚሊየን (127 ሚሊዮን የአሜ. ዶላር፤ የሀገር ውስጥ ምርት/GDP 0.1%) ያስገኙ ሲሆን በአጠቃላይ ገቢው በጥሬ ገንዘብ ወደ ሆቴልና ሬስቶራንት፣ መጓጓዣና ኮሚኒኬሽኖች እና የሕዝብ አስተዳደር ኢንዱስትሪዎች የገባ ነው። በጥናቱ ውስጥ የኢትዮጵያ አነስተኛ የመዝናኛ አደን ኢንዱስትሪ አስተዋፅኦ ከግምት የሚገባ አልነበረም።

ከዚህ በተጨማሪ ከነዚህ የመዝናኛ ጥቅሞች ሌላ የኢትዮጵያ ደኖችን ለሕዝቦቿ ደህንነት መንከባከብ ያለው ጠቀሜታ ከኢት. ብር 2.4 ቢሊየን (360 ሚሊየን የአሜ. ዶላር) ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ጠቀሜታ አለው። በመርህ ደረጃ ይህ ጥቅም ከጂዲፒው ጋር ተጣጣሚነት የሌለው ሲሆን በጥናቱ ውስጥ በተለየ ምድብ ውስጥ ተካቷል።



UN-REDD
PROGRAMME

Food and Agriculture Organization of the United Nations

UN DP
Empowered lives.
Resilient nations.

UNEP

ISBN No: 978-92-807-3605-2

DEP/2041/NA